# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

**ግንቦት 11 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ደብረማርቆስ በተቃውሞ ስትናጥ ሰነበተች፤**

**ህዝቡ ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ጋር እጅና ጉዋንት ሆኖ በአደባባይ ተቃውሞ ሲያሰማ ዋለ፤**

**መለስ ዜናዊ ባለስልጣናቱን የመቆጣጠሪያ አዲስ ስልት ተግባራዊ አደረገ፤**

**አባ ጳውሎስ እና ጳጳሳቱ ተፋጥጠው ሰነበቱ፤**

በየጊዜው ተማሪዎች ለሚያነሱት የመብት ጥያቄ ነፍጥ እያነገበ .....እየገደለ.....እያሰረና እያስፈራራ ምላሽ የሚሰጠው እብሪተኛው የወያኔ ቡድን ሰሞኑንም በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ ዘግናኝ እርምጃ መውሰዱ ታወቀ::

በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የተወሰደውን ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ በመቃወም የከተማዋ ነዋሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞና ብጥብጥ አንስተው ከወያኔ ታጣቂ ኃይሎች ጋር ግጭት መፍጠራቸውም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ወያኔ ለኮታ ማሙያ ብሎ በከፈታቸው ዩኒቨርስቲ ውስጥ የተሙዋላ የትምህርት መርጃ መሳሪያ.....የምግብ አቅርቦት.....ብቁ የሆኑ መምህራን ባለመኖሩ ተማሪው ይስተካከልልን ብለው ላነሱት የመብት ጥያቄ የወያኔ ቡድን ጭር ሲል አልወድም በሚል ስልጠናቸውን ባልጨረሱ ምልምል ወታደሮች የጅምላ ጭፍጨፋ እርምጃ መውሰዱ ታውቆዋል::

ተማሪው ብሶቱን በሰላማዊ መንገድ በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ ተቃውሞ እየገለፀ ባለበት ሰዓት ድንገት ከየት መጡ ሳይባል በብር ሸለቆ ወታደራዊ ማሰልጠኛ ውስጥ ገና በመሰልጠን ላይ ያሉ ምልምል ወታደሮች የእሩምታ ተኩስ በመክፈት ብዙ ተማሪዎች ላይ ጉዳት ማድረሳቸው ተረጋግጦዋል::

በተደጋጋሚ ግዜ ለዩኒቨርስቲው አመራሮች ጥያቄያቸውን ቢያቀርቡም ሰሚ እና አድማጭ ያጡት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች እሁድ ሚያዚያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም እኩለ ቀን ላይ በግቢው ውስጥ ተቃውሞ በማሰማት ላይ እንዳሉ በዩኒቨርስቲው አመራሮች በምስጢር ጥሪ የተደረገላቸው የብር ሽለቆ ምልምል ወታደሮች ድንገት ወደ ዩኒቨርስቲ ግቢ በመግባት የእሩምታ ተኩስ ከፍተው ቁጥራቸው የበዙ ተማሪዎችን ያቆሰሉ ሲሆን አንዱን ተማሪ ወዲያው ሊገድሉ እንደቻሉም በወቅቱ በተቃውሞው ላይ ከነበሩ ተማሪዎች የተገኘው ጥቆማ አጋልጦዋል:: በተፈጠረውም ግርግር የትምህርት ቤቱ መማርያ እና መመገቢያ አዳራሽ መስታወቶች እና ወንበሮች ከጥቅም ውጭ ሊሆኑ እንደቻለም የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

ግርግሩን ተከትሎ ተማሪዎች ከምልምል ወታደሮቹ ጥቃት በማምለጥ ወደ ከተማዋ ነዋሪዎች ውስጥ በመግባት ግዜያዊ መጠለያ ያገኙ ሲሆን በተጉዋዳኝ በመቶዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ታፍሰው ወዳልታወቀ ስፍራ መወሰዳቸውን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

ይህንኑ ግርግር እና ትርምስ ተከትሎ ታፈሰው የተወሰዱ ተማሪዎች ይመለሱ በሚል በግቢው ውስጥ የነበሩ ተማሪዎች ሰኞ ሚያዚያ 29 ቀን 2004 ዓ.ም ጠዋት «የታሰሩት ጉዋደኞቻችን ይፈቱ!» በሚል አደባባይ ወጥተው ተቃውሞ ማሰማት በጀመሩበት ወቅት ብሶት አዝሎ የተቀመጠው የደብረማርቆስ ከተማ ነዋሪ ግልብጦ ብሎ ከተማሪዎች ጋር በማበሩ የተደናገጡት የወያኔ ባለስልጣናት የፌዴራል ፖሊስ...የክልሉ ፈጥኖ ደራሽ.....የከተማዋ ፖሊስ እና ተጨማሪ የብር ሽለቆ ምልምል ወታደሮች በአራት አቅጣጫ ወደ ከተማዋ እንዲገባ ማድረጋቸውን ተከትሎ በተፈጠር ግጭት እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ነዋሪዎች ከፍተኛ ጉዳት ሊደርስባቸው እንደቻለ በወቅቱ ከነበሩ የዐይን እማኞች ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

እሁድ ሚያዚያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም በዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ በተከፈተው ተኩስ አንድ ተማሪ ወዲያው ሲደገል ፤5 ተማሪዎች በጥይት ተመትተው ክፉኛ የቆሰሉ መሆኑን እና ከአምስቱ የቆሰሉ ተማሪዎች መሀከል አንደኛው ኮማ ውስጥ እንደነበርና በማግስቱ እሱም ህይወቱ ሊያልፍ እንደቻለ የጠቆሙት የዩኒቨርስቲው ውስጥ አዋቂ ምንጮች ሌሎቹ ክፉኛ ጉዳት ስላጋጠማቸው ለህክምና ወደ አዲስ አበባ እንዲሄዱ መደረጉንም አብራርተዋል::

በደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ የተጀመረው የተማሪዎች ተቃውሞ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ ውስጥ ውስጡን ቀጥሎ የሚገኝ ከመሆኑም በላይ በምስጢር ተመልምለው ለወያኔ ያደሩ ተማሪዎች በስተቀር በግቢው ውስጥ ተማሪዎች እንዳልገቡም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልጾዋል::

በዩኒቨርስቲው ግቢ ውስጥ እና በከተማዋ አደባባዮች ተደብድበው ጉዳት የደረሰባቸው ተማሪዎች በከተማዋ ነዋሪዎች ትብብር በየቤቱ ተኝተው እንክብካቤ እየተደረገላቸው ሲሆን ወያኔ ግን በቤታቸው አስጠግተው ያሉትን ነዋሪዎች የተቃዋሚ ተባባሪ በሚል እያስፈራራ እንዲያስወጡዋቸው ውስጣዊ ቅሰቀሳ እንደጀመረም የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በአሁኑ ሰዓት ደብረ ማርቆስ ከተማ በህዝቡ ቁጣ እና በወያኔ ታጣቂ ኃይሎች ጥበቃ ተወጥራ የምትገኝ ሲሆን የፌዴራል ፖሊስ ፤የክልሉ ተወርዋሪ ፈጥኖ ደራሽ፤የከተማዋ ፖሊስ እና መልምል ወታደሮች ከተማዋን በመሳሪያ ጭምር ወጥረው ህዝቡን መውጫና መግቢያ አሳጥተውት እንደሚገኝ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ይገልጻል፡፡

ደብረማርቆስ ዩኒቨርስቲ ተቃውሞ ከመጀመሩ አንድ ሳምንት በፊት በጎንደር እና በባህርዳር ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ ተቃውሞ ተቀስቅሶ ተማሪው ብሶቱን አደባባይ ወጥቶ እንዳያሰማ በፌዴራል ፖሊስ ዙሪያቸውን ተወጥረው እንደሰነበቱ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚነሱ ጥያቄዎች እና ተቃውሞ እየደነገጠ የመጣው የወያኔ ቡድን ለነባር እና አፍለኛ ለሆኑ ካድሬዎቹ ስውር እና ምስጢር በሆነ መልኩ ልዩ ስልጠና እየሰጠ መሆኑ ታወቀ፡፡

በመላ ሀገሪቱ ለተነሳው የሙስሊሙ እምነት ጥያቄ .....የኑሮ ውድነት ከዕለት ወደ ዕለት እያደገ እና እየናረ መምጣቱ...... የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች የሚያነሱት ጥያቄ እና ተቃዋሚ ኃይሎች ህዝቡን እያነሳሱ በመሆኑ የተደናገጠው የወያኔ ቡድን እነዚህን ጥያቄዎች ለማፈን ብሎም ጨርሶ ለማጥፋት በሚል ለከፍተኛ ካድሬዎቹ ስውር እና ምስጢራዊ ስልጠና እየሰጣቸው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

በተለይ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ያነሳው ጥያቄ ከግዜ ወደ ግዜ እየተስፋፋ በመምጣቱ የተደናገጠው ይሄው ዘረኛ ቡድን ጥያቄውን ለማዳፈን እና ለማጥፋት ብሎም መጪው የአዲስ አበባን ምርጫ ለመቆጣጠር ህዝቡ ተቃውሞ እንዳያሰማ ለማድረግ የሚያስችል ስልጠና እየተሰጣቸው መሆኑ ከሰልጣኝ ካድሬዎች ጥቆማ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል፡፡

አንድ ለአምስት በሚለው መቆጣጠሪያ ስልት የተጀመረው የወያኔ ረግጠህ ግዛ ፖሊሲን የበለጠ ለማጥበቅ እና ህዝቡን ለመጨፍለቅ በማሰብ እየተሰጠ ያለው ይሄው ስልጠና ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ተውጣጥተው ለመጡ ከፍተኛ ካድሬዎች ሲሆን በአሁኑ ሰዓትም አዲስ ምደባ እየተሰጣቸው ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ መሰማራታቸው ታውቆዋል፡፡

በየቀኑ ከፍተኛ የአበል ክፍያ እየተሰጣቸው እና ምግብ ባሉበት መሰብሰቢያ አዳራሽ ድረስ እየመጣላቸው ያሉት ሰልጣኝ የሆኑት ከፍተኛ ካድሬዎቹ ከመለስ ዜናዊ ተነድፎ በወጣ አዲሱ ስልት ተጠምቀው በህዝቡ ላይ ተግባራዊ ለማድረግ እየሰሩ ሲሆን የየክልል ፕሬዝዳንቶችንና ምክትል ፕሬዝዳንቶችን ጭምር የመቆጣጠር እና የመሰለል ስልጣን ሁሉ እንደተሰጣቸው ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በቅርቡ ሙስሊሙን ህብረተሰብ ለመቆጣጠር ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ በወጣ ትዕዛዝ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ቢሮ ባዘጋጀው አዲስ ስልት መሰረት ተግባራዊ እየተደረገ ሲሆን ሙስሊሙ አንድ ሆኖ ተቃውሞውን እንዳያሰማ በተለያዩ ስልቶች እና በችግሮቹ እየገቡ ለመከፋፈል እየሰሩ መሆኑንም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በአንድ ቤተሰብ ጭምር ዘልቆ እየገባ ባልን ከሚስት .....ልጆችን ከወላጆች ለመከፋፈል እጅግ ሰይጣናዊ በሆነ መንገድ ከተቻለ በገንዘብ ካልሆነ በማስፈራራት እየሰሩ ያሉት የወያኔ ደህንነቶች በጥቅም፤በማግባባት ፤በማስፈራራት፤ኃይል በመጠቀም የሚሉት ስልቶችን ተግባራዊ ማድረግ መጀመራቸውም ታውቆዋል፡፡

እንደ ሙስሊሙ ህብረተሰብ ለመከፋፈል እና ለመቆጣጠር የደኢህዴን እና የኦህዴድ ከፍተኛ አመራሮችን ለመቆጣጠር ብሎም ለመሰለል የተላኩት የብአዴን እና የህወሀት አዲስ አፍለኛ ካድሬዎች ቀጥታ ግንኙነታቸው ከመለስ ዜናዊ እና ከበረከት ስምኦን ጋር ብቻ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ሰሞኑን በተሰጣቸው አጭር ኮርስ መሰረት የተሰጣቸውን ግዳጅ በአጭር ግዜ ተግባራዊ አድርገው ሪፖርት እንዲያቀርቡም ተብሎ መመሪያ እንደተሰጣቸው ተጠቁሞዋል፡፡

መቀመጫውን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ያደረገው የኦህዴድ የበላይ ጠባቂው ገብረ ተንሳይ ወ/ተንሳይ የተሰኘው የህወሀቱ ባለስልጣን ኦሮሚያን በልዩ መቆጣጠሪያ ስልቱ እና በተመደቡለት አፍለኛ ካድሬዎቹ አማካኝነት እያስተዳደረ እና እየመራ ሲሆን ደኢህዴንንም በተመሳሳይ ተክላይ በተባለ የህወሀት ከፍተኛ ካድሬ አማካኝነት መለስ እየተቆጣጠረ መሆኑን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ያብራራል፡፡

በኦህዴድ እና በኦሮሚያ ላይ የበላይ ሆኖ የተሾመው ገብረተንሳይ የተባለው የህወሀት ሰው ኦህዴዶችን እንቅልፍ እየነሳና እያስፈራራቸው ሲሆን ባለፈው ሳምንት ከአዲስ አበባ ወደ ወለጋ ልዩ ስምዋ ቤጌ ወደምትባለው መንደር በመጉዋዝ ላይ እንዳለ መኪና ተገልብጦ አደጋ የደረሰበትን የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረውን ዘላለም የተሰኘው ግለሰብ ከነቀምት በልዩ ቻርተር አውሮፕላን አንድ ሚሊዮን ብር ተከፍሎለት ወደ አዲስ አበባ በመምጣቱ ለምን አልተነገረኝም በማለት በባለስልጣናቱ ላይ ስድብ እና ማስፈራሪያ ሲሰነዝርባቸው እንደነበረ ዘገባው ጨምሮ ገልጾዋል፡፡

የመለስ ቅርብ ናቸው በተባሉት ግለሰቦች አማካኝነት መላ ሀገሪቱዋን እየተቆጣጠሩ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለይ የክልል ባለስልጣናቶችን በስውር እንዲሰልሉ ከመደረጉም በላይ እንዳስፈላጊነቱ ትዕዛዝ ሊሰጡዋቸው እንደሚችል ተጠቁሞዋል፡፡

በቅርቡ ለድሬዳዋ ከተማም አዲስ በስውር የሚመራና የሚቆጣጠር ወጣት አፍለኛ ካድሬ የተመደበ ሲሆን ምደባው በመለስ ዜናዊ ምስጢራዊ ደብዳቤ መሆኑንም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

አስቂኙና አስገራሚው ነገር ብአዴንና ህወሀቶችንም ለመቆጣጠር በተመሳሳይ ከራሳቸው ውስጥ ለመለስ ዜናዊ እና ለበረከት ስምኦን ይቀርባሉ በተባሉ አፍለኛ ካድሬዎች አማካኝነት እየተቆጣጠሩ ቢሆንም እንደ ደኢህዴንና ኦህዴድ ውጤታማ አለመሆኑንም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

በሌላ ዜና ለነፍሳቸው ሳይሆን ለስጋቸው ......ለዓለማዊው ሳይሆን ለምድራዊው ......ህይወት ተገዥ የሆኑት የወያኔ ቡድን አባል አባ ጳውሎስ ሰሞኑን በቤተክህነት ባነሱት የተለመደ ሽፍጥ ትርምስ ተፈጥሮ መሰንበቱን ከቤተክህነት አከባቢ የደረሰን ዘገባ ገለጸ፡፡

በሰሞኑ በተደረገው መደበኛ የሲኖዶሱ ስብሰባ ላይ እንደሌላው ግዜ ሁሉ በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ እየፈፀሙ እና እየሰሩ ያሉት ተንኮል እና ሸፍጥ እንዳይጋለጥ ለማድበስበስ ሲሉ በፈጠሩት ግርግር በጳጳሳቱ እና በእሳቸው መሀከል ከፍተኛ ብጥብጥ ተፈጥሮ መሰንበቱ ታውቆዋል።

ከእምነት ይልቅ ፖለቲካ.....ከፆም ይልቅ መንደላቀቅ.....ከውሀ ይልቅ ውስኪ.....ከጥሬ ቆሎ ይልቅ ጮማ ስጋ...... መርጠው የሚገኙት አባ ጳውሎስ የአንድ ጎሳ ተወላጆችን ብቻ ሰግስገው ቤተክህነትን ሙሉ ለሙሉ ከመቆጣጠራቸውም ባሻገር በህዝበ ክርስቲያኑ ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል ሸፍጥ እየሰሩበት በመሆኑ ጳጳሳቱ ክፉኛ ቁጣቸውን ሲያሰሙ ያሳለፉበት ሳምንት እንደሆነ የቤተክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አስረድተዋል።

የትግራይ ተወላጆችን ያውም የአድዋ ብቻ የሆኑትን እየመረጡ እና እየሰበሰቡ የሚገኙት አባ ጳውሎስ ለሚሰሩት ሀገራዊ እና ህዝባዊ በደል ሽፋን ሰጪ ሆነው በመገኘታቸው በቤተክህነት የሚሾምና የሚቀመጠው በጎሳ ሳይሆን በችሎታ ሊሆን ይገባል በማለት ጳጳሳቱ ጥያቄ በማንሳታቸው የተበሳጩት አባ ጳውሎስ ለአንድ ቀን ተኩል ስብሰባው እንዲሰረዝ እና እሳቸው ባሰቡት መንገድ እንዲሆንላቸው በሚል በተፈጠረ አለመስማማት ከፍተኛ ውዝግብ ተነስቶ እንደነበር የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ ጥቆማ አብራርቶዋል።

በተደጋጋሚ ግዜ ሲኖዶሱ የሚያስተላልፈውን ውሳኔና ትዕዛዝ ተግባራዊ አያደርጉም.....ጳጳሳቱን በዘር እና በጎጥ ለመከፋፈል ከፍተኛ ስራ እየሰሩ ነው.....ከመንፈሳዊ ስራ ይልቅ የፖለቲካ አካሄድ ይታይብዎታል......ዘረኝነት እና አድልኦ በቤተክርስቲያናችን ውስጥ እንዲነግስ እየሰሩ ይገኛሉ......የህዝበ ክርስቲያኑ ሀብት እና ገንዘብ የት እንደሚገባ በውል አይታወቅም ......የተጀመረውን የእርቅ እንቅስቃሴም ለማስቆም ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ .....የሚሉና ሌሎች ወሳኝ የሆኑ ጥያቄዎችን ጳጳሳቱ በማንሳታቸው የተበሳጩት አባ ጳውሎስ ይሄንን የሚያስወሩብኝ እኔን የሚጠሉና ውጭ ሀገር የሚገኘውን ሲኖዶስ የሚደግፉ ናቸው በማለት ምላሽ እንደሰጡም ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ አብራርቶዋል።

በተለይ ይላሉ ውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በተለይ አባ ጳውሎስ የሲኖዶሱን ትዕዛዝ እና ውሳኔ በመጣስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የልማትና ተራድኦ ኮሚሽን የሆኑት አቡነ ሳሙኤል ላይ የተለያዩ አደናቃፊ የሆኑ እርምጃዎችን እየወሰዱ ሲሆን ይሄም ከሲኖዶሱ እውቅና ውጭ በመሆኑ ሊታረም ይገባል መባሉን ጠቁመው በአቡነ ሳሙዔል ፊርማ ይንቀሳቀስ የነበረው የኮሚሽኑ ገንዘብ እንዲቆም በመደረጉ በቤተክህነት ሰራተኞች ጭምር ትልቅ ግጭት ፈጥሮ እንደነበረም ምንጮቹ ገልጸዋል።

እስከ ዛሬ በኮሚሽኑ ቼክ ላይ የሚፈርሙት አቡነ ሳሙዔል የነበሩ ቢሆንም አባ ጳውሎስ በምስጢር ለባንኮች ደብዳቤ በመጻፋቸው በእሳቸው ፊርማ ገንዘብ እንዳይንቀሳቀስ መደረጉን ተከትሎ ጳጳሳቱ በአባ ጳውሎስ ላይ ተቃውሞ ማሰማታቸውንም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል።

ሲኖዶሱ አባ ሳሙዔልን የኢትዮጵያ ኦርቶደክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተራድኦና ልማት ኮሚሽን ኮሚሽነር አድርጎ የሾማቸው መሆኑ እየታወቀ አባ ጳውሎስ

በምስጢር ለተለያዩ መንግስታዊና ለሌሎች ክፍሎች ከኃላፊነታቸው እንደተነሱ የሚገልፅ ደብዳቤ በመጻፋቸው ክፉኛ ቁጣን በመቀስቀሱ ውዝግቡ ተካርሮ እንደሰነበተም ከውስጥ አዋቂ ምንጮቹ የተገኘው ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡